ነሐሴ 2013
ቅጽ ፩ ቁጥር ፪

# ንስንስ

ትኩረቷን በLBTQ ላይ አድርጋ በየሩብ ዓመቱ የምትታተም መጽሔት

Nisnis - quarterly magazine focusing on LBTQ issues



# ኩራት

አታሚ/Publisher
QUEER ETHIOPIA
ኩዊር ኢትዮጵያ




# የራስዎን ድምፅ ያድምጡ

www.soundcloud.com/ethioqueer

# ንስንስ

ቅጽ ፩ ቁጥር ፪

በየሩብ ዓመቱ የምትታተመው ንስንስ
በኢትዮጵያ እና በዳያስፖራ የሚገኙ LBTQ
ጉዳዮች ላይ የምታተኩር መጽሄት ናት : :

ለጥያቄዎች :
etqueerfamily@gmail.com

በኩዊር ኢትዮጵያ የታተመ
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
© ነሐሴ 2013

# ማውጫ


| | |
|---|---|
| 3 | የአርታዒያን መልዕክት |
| 4 | ኩራት በራሳችን አንደበት |
| 12 | የመጀመሪያ የኩራት ክብረ በዐል ተሞክሮዎ ምን ይመስላል? |
| 14 | የመጀመሪያ የኩራት ክብረ በዐል፥ ወደቤት መምጣት |
| 16 | መብረር በውስጥ ያለን የአርነት ሰንደቅ ዐላማ ማውለብለብ |
| 19 | የፕራይድ አጀማመር |
| 20 | የራሴ የግል መስቀል አደባባይ |
| 23 | የቀስተ - ደመና ሰንደቅ ዐላማ ታሪክ |
| 24 | አጋርነት "ኖርማልን" በድጋሚ ፍቺ መስጠት |
| 26 | በሕይወት ዘመናችሁ "ኩራት" እንደ ክብረ በዓል በኢትዮጵያ ውስጥ ሲከበር የምታዩበት ጊዜ የሚመጣ ይመስላቹኃል? |
| 30 | ድምፅ አልባ እውነቶች |




# QUEER ETHIOPIA

# ኲዊር ኢትዮጵያ

«ኲዊር ኢትዮጵያ» የተለያዩ ፆታዊና ወሲባዊ ዝንባሌ ላላቸው ኢትዮጵያዊ ኲዊር ሴቶች እንዲሆን ታስቦ በኲዊር ሴቶች የተመሠረተ አማራጭ ምኅዳር ነው። ይኸውም ሌዝቢያን፣ ባይሴክሽዋል ወይም ኤሴክሽዋል የሆኑ ሴቶችንንና ትራንስ ሴቶችን ያካትታል። ይህ ምኅዳር የኲዊር ማኅበረሰብ ታሪክ እና የሕይወት ልምድ ትልቅ ሥፍራ የሚይዝበት ነው። እንደ' ኲዊር ማኅበረሰብ የዕለት ተዕለት ሕይወታችንን ገጠመኞች፤ የተለያዩ ሰዎችን የግል ታሪኮች፤ ቃለ - መጠይቆች እንዲሁም ሥነ - ጥበባትን እንደምናካትት ተስፋ እናደርጋለን። ከነዚህ በተጨማሪም በኢትዮጵያ ውስጥ እና በዳያስፖራ ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ቤተሰቦች ራሳቸውን ሆነው የሚመጡበት የበይነ - መረብ ማኅበረሰብ መድረክ ሆኖ እንዲያገለግል ማስቻል ፍላጎታችን ብቻ ሣይሆን ጥረታችንም ጭምር ነው።


queerethiopia.com

ethioqueer

QueerEthiopia

etqueerfamily@gmail.com

# የአርታዒያን መልዕክት

ወደ ንሥንሥ መጽሔት ሁለተኛ ዕትም እንኳን በደኸና መጡ።

በዚህ ዕትማችን ትኩረት የምናደርገው "ፕራይድ" (ኩራት) እንደ ክብረ በዓልና በቀንተቀን ሕይወታችን ውስጥ ምን ማለት እንደሆነ ነው። በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጪ በዲያስፖራው ዓለም ያለን "LBTQ" ኢትዮጵያውያን እየተማርን ያደግነው የወደድነው ሰውና ማንነታችን ትክክል እንዳልሆነ ነው፤ ኅጢያትና አሳፋሪ ስሜት እንደሆነ ነው። እየሰማን ያደግናቸውን ተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ፣ ትራንስጀንደር፣ ባይ፣ ኩዊር ጠልነት በውስጣችን አለማስቀመጥ ከባድ ነው።

ስለዚህ እንዴት ብለን ነው ማን እንደሆንን መማርን ኀፍረት በሌለበት ስሜት ማዳበር የምንችለው? ራሳችንን መውደድና ማክበር እንዴት ነው የምንማረው? ራሳችንን እንዴት ነው የምናኀለብተው? የኩራትን ስሜት እንዴት ነው ማዳበር የምንችለው? "LGBTQ+" መሆን ከሚያስገድልበት ማኅበረሰብ ውስጥ ለወጣን ኩራት ምን ትርጉም አለው?

እነዚህን ጉዳዮች በሙሉ አንሥተናል እና ማኅበረሰባችን ኩራትን የሚገልጽበት ሰፊና የተለያየ ይዘት ያለው መረዳት አስደንቆናል። ባደረግናቸው ቃለ-መጠይቆችና በሰበሰብናቸው የግለሰብ ታሪኮች መሠረት፤ "LBTQ" ማኅበረሰባችን ኩራትን ከአንድ ቀን ወይም ደሞ ከአንድ ወር ክብረ-በዓልነት ባለፈ እንደሚረዳው በጣም ግልፅ ነው።

ይህ ማለት ሰዎች ኩራትን እንደክብረ-በዓል ዐያዩትም ማለት አይደለም። ታሪካቸውን ካጋሩን ውስጥ አንዷ የመጀመሪያ የኩራት ተሞክሮዋን ስታስታውሰው "ለመጀመሪያ ጊዜ ኩዊር ሴት ሆኖ የደስታና የተሟላ ሕይወት መኖር የሚቻልበት ዕድል እንዳለ ነው የተሰማኝ" ትላለች። ፈጽሞ ይሆናሉ ብለን አስበን የማናውቅባቸው ነገሮች እውን መሆን እንደሚችሉ ያስታውሰናል።

ለሌሎች፤ ለዲያስፖራውዎችም ቢሆን፤ ኩራት ግልጽ ለመውጣት ድፍረቱን ባጡበት ሁኔታ ወይም ሌሎች ይናገሩብናልን ፍራቻ የራሳቸውን የሆነ ክብረ-በዓል እንዲመሠርቱ አበረታቷቸዋል፤ ያ ደሞ ጠንካራና አንፀባራቂ የኢትዮጵያ "LBTQ" ማኅበረሰብ በዲያስፖራው እንዲፈጥሩ ረድቷቸዋል።

አንዳንዶች (አዲስ አበባ መስቀል ዐደባባይ ላይ ብቻዋን በመውጣት ያከበረችውን ሴት ጨምሮ) የራሳቸውን ኩራት ለመመሥረት ሞክረዋል። መስቀል ዐደባባይ ላይ የወጣችበትን ምክንያት ስትጽፍ፤ ኩራትን እንደመታገያ መንገድ ጭምር እንደምትረዳ ነው። ይኸ ደሞ ኩራት እንደክብረ-በዓል ወሣኝ ቢሆንም ኩራት ተግባርም እንደሆነ ማስታወሻ አጽንዖት ነው። ኩራት በራሱ መንገድ የሚፈጠር ሣይሆን እኛ ወደዛ ለመድረስ በርትተን የምንሠራው ነገር ነው። ሕይወታችንን በተሟላ ሁኔታ ለመኖር በምንራመድበት ጊዜ የምንሠራበትና የምንሸርበት፣ የምንማርበትና የተማርነውን የምናስተካክንበት ጉዞ ነው።

ሌላው የኩራት መገለጫ የሆነው የተጋራነው ታሪክ፤ ኩራት ከክብረ በዓልም በላይ እንደሆነ ነው።

ቃለ-መጠይቅ ያደረግንላት ኢትዮጵያዊ "ሌዝቢያን" የሆነችው ፍቅር ኩራትን ስትገልጸው በየቀኑ የምታከብረው ነገር እንደሆነ ነው። እሷ እንደምትለው "ኢትዮጵያ ውስጥ እያለሁ ያሳለፍኩት ሕይወት የፈጠረብኝ የስሜት መቃወስና የተሞኩሮዬ መጠን፤ በየቀኑ ለራሴ ትክክል እንደሆንኩ እንዳረጋግጥ ምክንያት ሆኖኛል።"

በዚህ ጉዳይ ላይ የተለያዩ ኢትዮጵያውያንን ድምፅ አካተናል፤ የራሳችሁን ታሪክ በሌሎች ታሪክ ውስጥ ተንጸባርቆ ታገኙታላችሁ ብለን ተስፋ እናደርጋለን። ምናልባትም ኩራትን በአዲስ መንገድና ለማኅበረሰባችን ምን ማለት እንደሆነም ታዩበታላችሁ።

ተሣታፊዎቻችንንና በፍቃደኝነት ጊዜያቸውን ለቃለ-መጠይቅ፣ ታሪኮችን ለመጻፍ፣ ሀሳቦችን ለማካፈል፣ ፎቶ ለማንሣትና ስዕል ለመሳል የሰጡንን ከልብ እናመሰግናለን።

አንባቢዎቻችንንም ዕምነት ላይና ወሲባዊነት ላይ ትኩረቷን ያደረገችውን የመጽሔታችን የመጀመሪያ ዕትም ጊዜ ሰጥታቹ በማንበብ ለሰጣቹን ያልተቋረጠ አስተያየትና ግብረ-መልስ እናመሰግናለን። የናንተ ቀጣይነት ያለው ድጋፍ፤ ታታሪና ተራማጅ ኢትዮጵያዊ የ"LBTQ" ማኅበረሰብ በመፍጠር እናንተን በተሻለ ዐቅማችን ለማገልገል ያስችለናል።

መልካም ንባብ ይሁንላቹ

# ኩራት

# በራሳችን እንደበት

ቀስተ-ዳመናማ ጭምብል ከመንገዱ ላይ ገዝቼ ልክ ታክሲ ውስጥ ስገባ አጠለኩት። ከታክሲ ስወርድ አንድ ሰው እየተከተለኝ እንደሆነ አስተዋልኩ። አቆመኝና ጠየቀኝ “የማን ጭምብል እንደሆነ ታውቂያለሽ?”

“ከየት እንደገዛሁት እይጠየከኝ ነው?” ጥያቄውን በጭራሽ እንዳልተረዳሁት በማስመሰል ጠየኩት።

“አይ፤ እሱን እየጠየኩህ አልነበረም፤ ይኸኮ የነዛ ቆሻሾች ነው።”

“እነዛ ቆሻሻ ሰዎች እነማን ናቸው?” ብዬ ጠየኩትና እንዲ ብሎ መለሰልኝ “እነዛ ቆሻሾች እነማን እንደሆኑ አታውቂም? እነዛ ‘ሌዝቢያን’ እና መሰሎቻቸው ናቸዋ፤ ይመጡና ስልክ ቁጥርሽን ምናምን ይጠይቁሻል፤ ይህን ጭምብል ስላደረግሽ ከነሱ እንዳንዷ ነው የምትመስያቸው።”

ለራሴ እንዲ እያልኩት “እሱማ በጣም አሪፍ ነው የሚሆነው” ለሱ ግን ምክንያቱ ሌላ ሊሆን እንደሚችል፤ በመዋለ-ሕፃናት ውስጥም እንዳለ ነገርኩት። ከዛ ለምን እዚህ ጉዳይ ላይ ሊያተኩር እንደቻለ ጠየኩት።

“ይህ ከነሱ ጋር የተገናኘ ነገር ስለሆነ አሳፋሪ ነው። ምክንያቱም የነዛ ቆሻሻ ሰዎች ስለሆነ፤ ላንቺ ጥሩ አይደለም እናም ብትቀይሪው ይሻላል።” አለኝና ሄደ።

ኀብስት ኢትዮጵያዊ “pansexual” ነች። ይኸንን የቅርብ ጊዜ ታሪክ እየደገመች



“

**ደስታ ፈጥሮልኝ ነበር። በጣም ነፃነት ነበረው፤ [ጭምብሉን] አድርጌው በፖሊስ ጣቢያ ሁላ ዐልፌያለሁ። ጀግና የሆንኩ ያህል ነበር የተሰማኝ።**

ኅብስት



በአዲስ አበባ ጎዳናዎች ላይ የቀስተ-ዳመና ጭምብል ማግኘቷ እንዳስደነቃትና በአዲስ አበባ ጎዳናዎች ላይ ማድረግ መቻል የከፍታ ስሜት እንዳለው ትናገራለች።

“ደስታ ፈጥሮልኝ ነበር።” ትላለች። “በጣም ነፃነት ነበረው፤ አድርጌው በፖሊስ ጣቢያ ሁላ ዐልፌያለሁ። ጀግና የሆንኩ ያህል ነበር የተሰማኝ።”

ኢትዮጵያ ከ71 እንደ’ሀገር በጋራ ስምምነት ላይ የተመሠረተን የተመሳሳይ ፆታ ወሲባዊ ሁነቶችን ወንጀል አድርገው ከሰወዱ ሀገራት አንዷ ናት። ቀሪው የዓለም ክፍል “ኩራትን” እያከበረ፤ ኢትዮጵያውያን “LGBTQ+” የሆኑ ሰዎች ግን በጎዳና ላይ ወጥተው እንኳን የራሳቸውን ቀለም ማሳየት አይችሉም።

በዓለም ዐቀፍ ደረጃ የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ሴት እና ወንድ፣ “የባይሴክሹዋል”፣ “የትራንስጀንደር”



እና “የኩዊር” የኩራት ወር የሚከበረው የአሜሪካኑን የ1969 “Stonewall uprising” ለማስታወስ ሲባል በየዓመቱ በሰኔ ወር ላይ ነው። ኩራት በተለምዶ ተከታታይ ትዕይንቶች እና በቀለም ያሸበረቁ የLGBTQ+ እና የደጋፊዎቻቸው ትዕይንት-ሕዝብ የሚካተትበት ነው።

በኢትዮጵያ ውስጥ ኩራትን ማክበር አለመቻል እንዳለ ሆኖ፤ በዲያስፖራውም ሆነ በሀገር ውስጥ ያሉ ኢትዮጵያውያን ኩራትን የሚረዱትና የሚኖሩት በተለያየና በተወሳሰበ መንገድ ነው። አንዳንዶች ኩራት ላይ ታድመው ያውቃሉ፤ ሌሎች ደ’ሞ አንድ ቀን እታደማለሁ ብለው ተስፋ ያደርጋሉ፤ ለቀሪዎቹ ደ’ሞ ኩራት ቀን በቀን የሚያከብሩት/የሚኖሩት እንጂ ከአንድ ክስተት ጋር የሚያገናኙት አይደለም።

ዋናው የኩራት ክብረ በዓል ኢትዮጵያ ውስጥ ተካሂዶ ባያውቅም፤ አንዳንዶች በትንሽ ቡድኖች በመሆን፤ ሌሎች ደፋር የሆኑት ደ’ሞ በከተማዋ መውጫ ላይ የቀስተ-ዳመና ሰንደቅ ዐላማውን በማሳየት ኩራታቸውን ይገልጻሉ፤ ማንም ሳያያቸው ምልክቶችና በጎዳናዎች ላይ የሚተዉም አሉ።

ቁርጠኝነት ያለው የLGBTQ+ ማኅበረሰብ በሌለበት ሁኔታ ኢትዮጵያዊያን LGBTQ+ የሆኑ ሰዎች ኩራታቸውንና ማንነታቸውን በተለያዩ



መንገዶች ይገልጻሉ። ሌሎች ደ'ሞ ከኢትዮጵያ ውጭ በመሄድ ጭምር የኩራት በዓል ላይ ይታደማሉ።

ኑሮዋን አዲስ አበባ ያደረገችው ራሄል በኡጋንዳ በተከበረ ኩራት ላይ ለመታደም ዕድሉ ገጥሚታል። "የኩራት በዓል መሆኑ ግልጽ እንዲሆን የተደረገ አይመስለም፤ ይምስለኛል ለደኅንነት ተብሎ ነው።" ትላለች ሁኔታውን ስትገልጸው። "በሀይቁ ላይ አጭር የእግር እርምጃዎችን ማድረግ ነበር፤ በጣም ብዙ ሰው አልነበረም።"

አውሮፓ ውስጥ ከታደመችባቸው ሌሎች የኩራት በዓላት ጋር ስታነጻጽረው፤ ራሄል የኡጋንዳውን የዋናው ክብረ በዓል ስሜቱ እንዳይጠፋ ለማድርግ ኢ-ፍትሐዊ ሕጎችና የLGBTQ+ የሆኑ ሰዎች ራሳቸውን እንዲደብቁና እንዲወሥኑ የሚያደርጋቸውን አመለካከቶች መቃወሚያ እንደነበር ትገልጸዋለች።

ቤተሰቦቿ ገና በጣም በታዳጊ ዕድሜዋ ወደ አሜሪካ ይዘዋት የተሰደዱት አደይ በኒዮርክ ስለታደሙበት የኩራት በዓል ሲገልፁ በፍቅር ነው። ሌዝቢያን የመሆናቸው እውነት የፈጠረባቸው ምቾት በኩራት ላይ እንሪትታደሙ እንዳበረታታቸው ይገልፃሉ።

"ትልቅ ተሞክሮ ነበር።" ትላለች። "ፓርቲ ነበር የሚመስለው፤ እንዲ ዓይነት ክብረ-በዓል ማየት እጅግ ደስ ይላል።

የሚ ኑሮአቸውን በአሜሪካ ያደረጉ፤ ከሁለቱ ስርዓተ ፆታ ውጪ ያሉ "pansexual" ኢትዮጵያዊ ሲሆኑ ወሲባዊ ዝንባሌያቸውን ያወቁት በቅርብ እንደመሆኑ መጠን ራሳቸውን "baby gay" ብለው ነው የሚወስዱት።

“

**አንድ የምፈልገው ወሣኝ ነገር ቢኖር ማኅበረሰብ ነው፤ የLGBTQ ማኅበረሰብን ባልተከመደ ሁኔታ በተከታታይ ጥቃት እየደረሰበት እንደሆነ ይሰማኛል። ስለዚህ አጥብቄ የምፈልገው ነገር ቢኖር ይህ እንደማይሆን ዋስትና የሚሰጠኝ ማኅበረሰብ ነው።"**

**የሚ**

የዚህ አዲስ ግኝት የፈጠረው ብርታት በሜትሮፖሊታን ቦታ ውስጥ ለኩዊር የሚሆን፤ በተረጋጋ ሁኔታና ከነሱ ጋር ተስማምቶ የሚያኖራቸውን ቦታና ማኅበረሰብ መፈለግ ሆኖላቸዋል።

“ያንን እንድፈልግ የሚረዱኝ ጓደኞች ነበሩኝ” ይላሉ የሚ። እናም እዛው ቦታው ላይ በመሆን ነበር አዲስ ማንነቴን ያወኩት። እናም ‘እሺ፤ ይምስለኛል ትክክል ነኝ፤ በትክክለኛው አቅጣጫ ላይ ነኝ’ የሚለውን ለራሴ ያረጋገጥኩት።”

ምንም እንኳን በሚኖሩበት አካባቢ ኩራትን ለመታደም ቢችሉም፤ የቆዳ ቀለም ስብጥሩ ላይ ያለው ክፍተት፤ ቦታው ከሁለትዮሽ ስርዓተ ፆታ ውጪ ላሉ ጥቁር ስደተኞች ድምፅ ለመሆን ጭምር የተፈቀደ ቦታ እንዳይመስል አድርጎታል። ለየሚ “ኩራት” “LGBTQ+” ስለሆኑ ሰዎች ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን ፖለቲካውም ሆነ ሌሎች ልዩነቶች የሚንጸባረቁበት ቦታ ጭምር ነው።

“አንድ የምፈልገው ወሣኝ ነገር ቢኖር ማኅበረሰብ ነው፤ የLGBTQ ማኅበረሰብን ባልተለመደ ሁኔታ በተከታታይ ጥቃት እየደረሰበት እንደሆነ ይሰማኛል። ስለዚህ አጥብቄ የምፈልገው ነገር ቢኖር ይህ እንደማይሆን ዋስትና የሚሰጠኝ ማኅበረሰብ ነው።” ይላሉ።

ለአንዳንዶች ከኢትዮጵያ ውጭ መሆን ራሳቸውን በግልጽ እንዲያሳዩ




**“ሁለቴ የመገደል ያህል ነው። በግልጽ ለመውጣትና እንደዛ ያለ ነገር ለመሞከር እጅግ አስቸጋሪ ነው። ስለዚህ አለመታደል ሆኖ ኩራትን ለመታደም አልቻልኩም፤ ምክንያቱም የማውቀው ብቸኛ የኩራት በዓል በኔ አካባቢ ያለውን ነው። እዛ አካባቢ ብዙ ሰዎች ያውቁኛል ስለዚህ ለመታደም ደኅንነት አልተሰማኝም።**

**ፍቅር**

ዋስትና ወይም የብርታት ስሜት ይፈጥርላቸዋል ማለት አይደለም። ለፍቅር ምንም እንኳን ከሀገር ውጭ ብትኖርም እታወቃለሁ የሚለው ሥጋት እስካሁንም በኩራት በዓል ላይ እንዳትታደም አድርጓታል። የወጣችው ፍጹም ወግ አጥባቂ ክርስቲያንና በሚኖሩበት የስደተኞች ማኅበረሰብ ውስጥ በጣም ከሚታወቁ ቤተሰብ ነው።

ፍቅር ኢትዮጵያ እያለች አንድ ፓስተር ለእናቷ “የሆሞሴክሹዋል መንፈስ” አለባት ብሎ በመናገሩ “የለውጥ ሕክምና” (conversion therapy) ሁላ እንድትከታተል ተደርጋ ነበር። እናቷ ልጃቸው ላይ አለ የተባሉት መንፈስ እንዲወጣላት በሚል ለ21 ተከታታይ ቀናት ጸሎት ሞክረዋል። ይህ አሰቃቂ ተሞክሮ ወግ አጥባቂ ፕሮቴስታንት ቤተሰብ ውስጥ እንዳደገ ስለወሲባዊ ዝንባሌዋ እንዲሁም ተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪነቷን ለመቀበል ያደረገችውን ጥረት ፣ መረዳትና ጉዞ ቀርፆታል።

“ሁለቴ የመገደል ያህል ነው። በግልጽ ለመውጣትና እንደዛ ያለ ነገር ለመሞከር እጅግ አስቸጋሪ ነው” ትላለች ፍቅር። “ስለዚህ አለመታደል ሆኖ ኩራትን ለመታደም አልቻልኩም፤ ምክንያቱም የማውቀው ብቸኛ የኩራት በዓል በኔ አካባቢ ያለውን ነው። እና አባቴ የሚሠራው ደ’ሞ እዛው አካባቢ ነው፤ በጣም ይታወቃል። እዛ አካባቢ ብዙ ሰዎች ያውቁኛል ስለዚህ ለመታደም ደኅንነት አልተሰማኝም።”

የምትኖርበት አካባቢ ላይ ተቀባይነት ያለውና ለጥቃት የማያጋልጣት ቢሆንም፤ በኢትዮጵያዊ ቤተሰቦቿ ዘንድ ተቀባይነት የሌለው መሆኑ ለፍቅር በኩራት ላይ ለመታደም ከባድ አድርጎባታል።

ታዲያ መታደም እንኳን ባልቻሉበት ሁኔታ ኢትዮጵያውያን LGBTQ+ የሆኑ ሰዎች የኩራትን በዓል ትርጉም እንዲኖረው ለማድረግ ምን ምርጫ ይኖራቸዋል?

ለፍቅር እና እሷ በምትኖርበት አካባቢ ላሉት ኢትዮጵያውያን የLGBTQ+

> “ኩራት ከክብረ በዓልነት ያለፈ ብዙ ነገር አለው። ስለመለወጥ ነው፤ ልክ ውስጥሽ ዘልቆ የገባውን አስተሳሰብ እንደመለወጥ፤ መኖር የምትፈልጊውን ዓይነት ኑሮ በትክክል መኖር እንድትችይ።
>
> **አደይ**

ማኅበረሰብ፤ እነሱ በሚኖሩበት አካባቢ እንደሚዘጋጀው ዓይነት ትልቅም ባይሆንም የኩራት በዓል ማካሄድ ኖሮባቸዋል።

“የራሳችን የምንላቸው ትናንሽ ነገሮች ነበሩን፤ የራሳችን የምንለው ቦታ እንዲኖረን አድርገናል።” ትላለች በአካባቢው ላይ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የLGBTQ ማኅበረሰብ አባላት ጋር ኩራትን የተመለከተ መሰባሰብ ማድርግ የመቻላቸውን ታሪከ ስታወራ። ከኢትዮጵያውያን የLGBTQ+ ወዳጆች ጋር መሆን የፈጠረው ደስታ ለፍቅር ከትልቁ የLGBTQ+ እና ከኢትዮጵያውያን ማኅበር ጋር የመገናኘቷ ማዕከል ነው።

ምንም እንኳን ለየሚ የተለመዱት የኩራት በዓላት ትልቅ ቦታ ቢኖራቸውም፤ አሁን ላይ የኩራት ክብረ በዓላት ገብያውን የተቆጣጠሩት ቢሮክራቶች ተጠቃሚውን የሚይዙበት ሥርዓት ወደ መሆን እይተቀየረ ነው። ከዚህ አንጻር እሳቸው አካባቢ የሚከበረው የጥቁሮች የኩራት በዓል በተሻለ ተራማጅና በርግጥም ደስታ የተሞላበት ነው። በተጭማሪም “እርስ በራሳችን እንዴት መደጋገፍ እንደምንችልና ብዙ ወሣኝ ውይይቶች እንደሚኖሩን ተስፋ አደርጋለሁ።”

ለአደይ ኩራት ቅቡልነታቸውን የሚያረጋግጡበት አልነበረም። “ኩራት ለኔ የሆነ ቅቡልንቴን የማረጋግጥብት ሆኖ ዐያውቅም።” ይላሉ። “እንደኔ የምመርጠው ትንሽ ቡድን ነገር ነው። አጠቃላይ ያለው ፓርቲ የሚመስለውን ገጽታው ብዙም አልወደውም። ከወዳጆች ጋር ሲሆን ግን የሚያዝናና ነገር አለው።”

የኩራት ክብረ በዓላትን ማክበር አለመቻሉ ኢትዮጵያዊ የLGBTQ+ የመሆናቸውን ክብራቸውን ግን አላጎደለባቸውም። ኢትዮጵያውያን LGBTQ+ ኩራትን በተለያየን ደረጃ እንዴት መግለጽ እንዳለባቸው ተምረውታል።

“ከልቤ እንደማስበው ኩራት ማለት ማኅበረሰብ ነው። ምክንያቱም ወደኋላ ሄጄ የኩራትን አመሠራረት ሳስተውልና ዐመፅ የመሆኑን እውነታ ስረዳ፤ ለኔ ኩራት ማኅበረሰብና ትግል እንደማለት ነው። ስለዚህ ለኔ መሠረታዊ ነገር በማኅበር ሆነን በአንድነት በመታገል የሚቀበለን ማኅበረሰብ መፍጠር መቻል ላይ ነው።” ይላሉ የሚ።

ይህ ደ’ሞ የኩራት በዓልን በዓመት አንዴ ‘በኢትዮጵያ ውስጥና በዲያስፖራ ማኅበረሰብ ውስጥ ባሉ ኢትዮጵያውያን በጣም የተስፋፋው ተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ጠልነት ባለበት ሁኔታ’ ራስን መቀበል ያለውን ጠቀሜታ ከሚያስታወስ በዓልነት ያለፈ ነገር እንዳለው ነው።

ለኀብስት ኩራት ከሌሎች ከምታገኘው ቅቡልነት ይልቅ ውስጣዊ የሆነ ነገር እንደሆነ ነው የምትረዳው።

“ኩራት ለኔ ራስን መቀበል ነው፤ ከራሴ ጋር ነው የማገናኘው” ትላለች። “ኩሩ ሰው ብዬ የምትጠራቸው ሰዎች ራሳቸውን መቀበል የቻሉ ሰዎች ናቸው። በማንነታቸው የማያፍሩና ያለምንም ማፈር “እኔ የማስበው እንደዚህ ነው” ማለት የሚችሉ ናቸው። ያ ነው ለኔ ኩራት፤ ራስን ማግኘትና በግልፅ መኖር ደግሞ ተጨማሪ ነው።”

አደይ ኩራትን የሚረዱበት መንገድ የኀብስትንም ያንፀባርቃል። እናም ኩራትን በጣም ሰፋ አድርገው ነው የሚያስቡት።

“ይመስለኛል ኩዊር መሆን የመገለል ነገር አለው። ተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ጠልና መሰል አስተሳሰቦች ውስጥሽ ድረስ ዘልቀው ሲገቡ፤ ምን መሆን እንዳለብሽና ሌሎችስ ምን መሆን አለባቸው ብለሽ ስታስቢ፤ በተፈቀደበት ቦታ ላይን’ኳን ሆነሽ የመገለል ስሜት አለው። እዚህ ገዳቢ አስተሳሰብ ላይ ነው መሠራት ያለበት።” ይላሉ። “ኩራት ከክብረ በዓልነት ያለፈ ብዙ ነገር አለው። ስለመለወጥ ነው፤ ልክ ውስጥሽ ዘልቆ የገባውን አስተሳሰብ እንደመለወጥ፤ መኖር የምትፈልጊውን ዓይነት ኑሮ በትክክል መኖር እንድትችይ።”

*(የዐርታዒ ማስታወሻ፡ የተሳታፊዎች ስም ማንነታቸውን ለመከላከል ተቀይሯል።)*

ኩሩ ሰው ብዬ የምትጠራቸው ሰዎች ራሳቸውን መቀበል የቻሉ ሰዎች ናቸው። በማንነታቸው የማያፍሩና ያለምንም ማፈር “እኔ የማስበው እንደዚህ ነው” ማለት የሚችሉ ናቸው። ያ ነው ለኔ ኩራት፤ ራስን ማግኘትና በግልፅ መኖር ደግሞ ተጨማሪ ነው።

ኅብስት





# ፕራይድ እንደ ኢትዮጵያዊ

## የመጀመሪያ የኩራት ክብረ በዐል ተሞክርዎ ምን ይመስላል?

### “ሰዎች በግልጽ ሲያከብሩና ራሳቸውን መቀበል መቻላቸውን ማየት እጅግ ነፃነት የሚሰጥ ስሜት ነበረው።”

የ2008 ዓ.ም. የኩራት ወር በዓል የመጀመሪያዬ ነበር። ልክ 20 ዓመቴን የያዝኩበትና ከኩዊርነቴ ጋር በዝምታ የምታገልበት ጊዜ ነበር። ኩዊር ነኝ? ምንስ ማለት ነው? እንዴትስ በግልጽ መኖር እችላለሁ?

ሁለት ታናናሽ ወንድሞች አሉኝ፤ ካንደኛው ጋር በጣም እንቀራረባለን። አንድ ቀን ልነግረው ወሠንኩ እናም በሱ ምላሽ በጣም ነበር የተደናገጥኩት። ትንሽ ቢገረምም ስለነገርኩትና ሚሥጥሬን ሊጠብቅልኝ እንደሚችል ርግጠኛ ስለሆንኩበት በጣም ነበር ደስ ያለው፤ እናም የመጀመሪያዬን የኩራት ወር ለማክበር ስሄድ አብሮኝ በመሄድ ድጋፉን አሳየኝ። አጋጣሚ ሆኖ የሱ የከፍተኛ ትምህርት ምርቃትና ለእኔ የመጀመሪያዬ የሆነው የኩራት ቀን ተመሳሳይ ቀን ነበር የዋሉት፤ ያም ቀኑን የክብረ በዓልና ደስታ የተሞላ አደረገው።

ሰዎች በግልጽ ሲያከብሩና ራሳቸውን መቀበል መቻላቸውን ማየት እጅግ ነፃነት የሚሰጥ ስሜት ነበረው። እኔና ወንድሜ የበዓሉ ታዳሚዎች በጎዳናው ላይ እየሄዱና በቡድን ሆነው አስቂኝ ትዕይንቶችን በመፍጠር ሊቀበሉን ባልፈቀዱት ላይ ሲያለምጡ በመገረም ውስጥ ሆነን ነበር ያየናቸው። ኩዊር ሴት ሆኖ ደስተኛ ሕይወትን መኖር እንደሚቻል ለመጀመሪያ ጊዜ ተሰማኝ። ከእናቴ እሰማው የነበረው ሁሉ ኩዊር ሰዎች ሕይወታቸው አሰቃቂ እንደሚሆኑ ነበር፤ በኩራት በዓል ላይ ያየሁት ግን ጥቁር የሆኑ ሰዎች ከቤተሰቦቻቸው ጋር በመገኘት በሙሉ ፍቅር ሲያከብሩ ነበር። ሁኔታው ወደፊት እንደ አንድ ኢትዮ-አሜሪካዊት ኩዊር ሴት ራሴን ለመግለጽ የነበረብኝን ፍርኀት ቀነሰልኝ።

## “ነጮች በበዙበት ውቅይኖስ ውስጥ ምንም የማልታይ ሆኖ ተሰማኝ።”

2009 ዓ.ም. ላይ ነበር ለሴት መሳብ እንዳለኝ በመጨረሻም የተረዳሁት፤ በሕይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ፤ ያን ማወቄ ምንም አልፈጠረብኝም።

ያም ሆኖ ግን፤ ማንነቴን ደብቄ የተረጋጋ ሕይወት ለመኖር ወሠንኩ፤ ብቻዬን የምሆንበት ወይንም ደ'ሞ ወንድ ነክ ተብሎ ፆታው ከተወሠነለት ሰው ጋር የፍቅር ጊዜ እያሳለፍኩ ነገር ግን ሳላስጠጣ ደ'ሞ ሴቶችን መፈለግ ነገር። ውስጤን የዘለቀው ፍርኀትና ማፈር ግን ተፅዕኖው ከመቼውም በላይ ነበር።

በጊዜው፤ አንድ ለተቃራኒ ፆታ ፍላጎት ያላትና በHIV/AIDS ላይ ለሚሠራ ተቋም አብራኝ ትሠራ የነበረች፤ በዛ ዓመት ለሚካሄደው የኲራት ትዕይንተ ሕዝብ ከሥራ ባልደረቦቿ ጋር አብራ ትገኝ ነበርና አብሬያቸው እንድሄድ ጋበዘችኝ። አዲስ ሳገኘሁት ማንነቴ ፍጹም የምለው አጋጣሚ ነበር፤ ደኅንነቴ ተጠብቆ መሣተፍ መቻል። እጅግ ደስተኛ ነበርኩ። አስበው የነበረ ነገር ነው፤ ቅርቤ የሆነ ማኅበረሰብ እንደማገኝ፤ ሁሌም በሚሥጥራዊነት ተሰፋ አደርገው እንደነበር ወደፊት ለመራመድና ማንነቴን እንዳገኝ እንዲረዳኝ።

ይልቁንም፤ ነጮች በበዙበት ውቅይኖስ ውስጥ ምንም የማልታይ ሆኖ ተሰማኝ። ሁሉም የራሱ ቡድን ወይም ጓደኛ ነበረው፤ እናም እዛ በመገኘታቸው በጣም ደስተኛ ይመስላሉ። ከባድ ኀፍረትን ተሸክሜ ደስተኛ አልሆንም፤ ልሆንም አልችልም። እንደኔ የሆነና ሊመራኝ፤ ይህን ተሞክሮ ሊጋራኝ የሚችል ሰው አላውቅም።

ኮሌጅ እያለሁ ኢትዮ-አሜሪካዊ የሆኑ ኲዊሮች ማየቴን አስታውሳለሁ፤ እናም በሁሉ ነገራቸው የነበራቸውን ግልጽነት እቀናበት ነበር። በኲራት ጊዜ ፀጉራቸውን ፒንክ ተቀብተው እንዴት ባለ ነፃነት ራሳቸውን እንደሚገልጹ፤ ከነሱ ጋር ራሴን ሳነጻጽረው የሆነ አሸቦነት ተሰማኝ፤ ፀጉረ ልውጥ የሆንኩ ዓይነት ነገር።

እነዚህን ፍርኀቶቼን የማስተናግድበት ልምድ ማጣቴ ሁኔታውን አስፈሪ አደረገው። ለዓመታት፤ የፍቅር ፍላጎት ሊኖረን የሚገባው ከተቃራኒ ፆታ ጋር ብቻ ነው የሚለው ዓለም ውስጥ በማስመሰል ከመኖሬ እውነታ ጋር ስታገል ኖሬያለሁ፤ እናም ለኲዊር ዓለም የበቃሁ አልነበርኩም። እስከዛ ድርስ በየትኛውም የኲራት በዓል ላይ ተገኝቼ አላውቅም።

የመጀመሪያ ኲራት ተሞክሮዬ እጠብቀው እንደነበረው አስደማሚ ዓይነት አልነበረም። ወደራሴ እንድመለስ ነው ያደረገኝ። ሁኔታውን ካየሁ በኋላ፤ ስለLGBTQIA+ የጋራ የሆነው ሥፍራ ላይ ግልፅ የሆነ ሃሳብ ያለመኖሩ ያመጣው ቅሬታ፤ ግለሰቦች ከኲዊሮች ጋር ያላቸውን ያልጠራ ግንኙነት ላይ ትኩረት አድርጌ እንድከታተል አደረገኝ። እነዛ ግኑኙነቶችና ወዳጅነቶች የሚያስፈልገኝና ስፈልገው የቆየ ዓይነት ማኅበረሰብ ነበር። ስለኲዊርነት፣ ስለወሲባዊነት እና ፆታ ለማወቅ እንድጥር የሚያስችለኝን ምቹ ሁኔታ ፈጠረልኝ። ኀፍረት፣ ፍርኀት እና ኀዘን ውስጥ እርስ በራሳችን እንደጋገፋለን። ከምንም በላይ በቂ ኲራት በማይሰማኝ ጊዜ እንኳን ጥሩ ስሜት እንዲኖረኝ ያደርጉኛል።

### “ኲዊር ማህበረሰብን ማየት እንዴት እንባ ያስመጣ! የደስታ እንባ!”

ለመጀመሪያ ጊዜ ፐራይድ የተካፈልኩት ከሃገር የመውጣት ገጠመኙ ተፈጥሮ ነው፤ ከአንድ አምስት ስድስት አመት በፊት። አንድ የአውሮፓ ከተማ ላይ በጣም በትልቁ ደምቆ የተከበረበት ቀን የመጀመሪያው ትውስታዬ ነው።

ልክ አዲስ አበባ ላይ እንዳለው እንደታላቁ ሩጫ ዋና ጎዳናዎችን በተለያዩ ሙዚቃ እና ዳንሶች ታጅቦ ኲዊር ማህበረሰብን ማየት እንዴት እንባ ያስመጣ! የደስታ እንባ!

ነፃነት ለካ እንደዚህ ደስ ይላል፤ ራስን ሆኖ መኖር! ከጥግ እስከጥግ ከተለያዩ ህብረቀለማት አሸብርቃ ማየት! ማክበር መከበር ደስስስስ ይላል።

## የመጀመሪያ የኩራት ክብረ በዐል፥

# ወደቤት መምጣት

የመጀመሪያዬ ኩራት። 18 ዓመቴ ነበርና ለኑሮ ወደ አሜሪካ ገና መሄዴ ነበር። በእኛ ሀገር ተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪነት ቦታ የማይሰጣቸው ጉዳዮች ናቸው። ለውይይት እንኳን የሚቀርቡ አልነበሩም። ከቀረቡም በጣም ባጭሩና የድፍረት አስተያየት ነው የሚሆነው። አሜሪካን በሄድክ በስድስት ወሬ ግን ስለኩዊርነት ብዙም ግንዛቤ ያልነበረኝ ልጅ የኩራት በዓልን ወደ መታደም ተሸጋገርሁ።

ነጮችና ቀስተ-ዳመና ባንዲራ ከሚበዛበት የሰው ውቅያኖስ ውስጥ ሞተር ሳይክል ላይ የተቀመጡ የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ሴቶችን አስታውሳለሁ። አንዳንዶቹ ከላይ ምንም ያላደረጉና የጡታቸው ጫፉ ብቻ የተከለለ ናቸው። በሙሉ ዐቅማቸው ድምፃቸውን በጎዳናው ላይ እያሰሙ ወደ ትዕይንተ ሕዝቡ አመሩ። አብዛኞቹ በማህበረሰባችን በተለምዶ “ወንዳወንድ” የሚባሉና የስርዐተ ፆታቸውንና ወሲባዊ ዝንባሌያቸውን በቀላሉ መግልጽ መቻላቸውና ምቾታቸው ዓይኔን ከነሱ ላይ መንቀል እንዳልችል ነበር ያደረገኝ።

“Drag queens” (በተለምዶ “እንደ’ሴት” የሚባለውን አለባበስ የለበሱ ወንዶች እና ትራንስ ወንዶች) ከነካባቸው ዐየሁ፤ ይህ እንደሚቻል አስቤው ሁላ ዐላውቅም። ይሄ እንደሚቻል እንዴት አላሰብኩም?

አስታወሳለሁ በትዕይንት-ሕዝቡ ወቅት በከፍተኛ ሁኔታ የሚሰማ ድምፅ ከግርግር ውስጥ ይሰማኛል። “PFLAG (Parents and Friends of Lesbians and Gays)” የድጋፍ ሠልፍ እያደረጉ ነበር። ከያዙት መፈክር ውስጥ “የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ወንድ ልጃችን ምንም ዓይነት ችግር የለበትም።”፣ “የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ የሆኑትም ሆኑ ያልሆኑት ልጆቻችን ምርጦች ናቸው።” እና “የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ሴት የሆነችውን ልጄን እወዳታለሁ።”

የያዟቸው መፈክሮችና ከዛ ጀርባ ያለውን ስሜትና መልዕክት ለመረዳት የነገሩ አጠቃላይ ምስል እንዲኖረኝ አላስፈለገኝም። የPFLAG የድጋፍ ሠልፍ ትዕይንተ-ሕዝብ ሁልጊዜም በኔ በኩል ሲያልፉ ጮክ ብዬ ድጋፌን ማሳየት ጀመርኩ። ይሄ ከትኛውም ኩራት በዐል ደስ የሚለኝ ሆኖ ቀርቷል። እናት፣ አባትና ሌሎች ቤተሰቦች እንዲህ ዓይንት ገደብ የለሽና የሚታይ ፍቅርና ድጋፍ ለሚወዷቸው ሲያሳዩ ማየት ሁሌም ልብን የሚነካ ነገር አለው።

በአሜሪካ ትንሽ ከተማ እንደመኖሬ መጠን ከLGBTQ ማኅበረሰበ ጋር ያለኝ ግንኙነት እዛ ጋር ተገድቧል፤ ስለዚህ ከሌሎች ኩዊር ጥንዶች ጋር የማሳለፍ አጋጣሚው አልነበረኝም። ተመሳሳይ ፆታ ያላቸው ሰዎች መሳሳምና እጅ ለእጅ መያያዝ የወጣሁበት ባህል ውስጥ የለም እናም ሰዎች በግልጽና ዕየታዩ ሲፋቀሩ ማየት የሆነ አዲስ ነገር አለው። ሰዎች በግልጽ ፍቅራቸውን ሲገላለጹ ማየት ትኩረቴን በሁለት ምክንያት ስቦታል፤ አንድም ዕያየሁት ያደኩት ነገር ባለመሆኑ እና በአሜሪካ ጎዳናዎችም’ኳ ላይ ሆነ እኔ በምኖርበት ትንሽዬ ከተማ ላይ ራሳቸውን ችግር ላይ እየጣሉ ነው ብዬ ስላሰብኩ ነው።”

የ18 ዓመት ልጅ ነበርኩ ሴቶች ከላይ ምንም ሳይለብሱና ወንዶች በማህበረሰባችን በተለምዶ “የሴት ልብስ” የሚሏቸውን ለብሰው - የስርዐተ ፆታ ውስብስብነት ገና ቋንቋ ስላልነበረኝ - ማየት ቀልቤን እንደሳበው ሁሉ የኩራት ክብር በዓልም ቀልቤን ምናልባትም በዕኩል ደረጃ ነው የሳበው። የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ጠል እንድሆን ተምሬ

> “
> **የ18 ዓመት ልጅ ነበርኩ ሴቶች ከላይ ምንም ሳይለብሱና ወንዶች በማህበረሰባችን በተለምዶ “የሴት ልብስ” የሚሏቸውን ለብሰው - የስርዐተ ፆታ ውስብስብነት ገና ቋንቋ ስላልነበረኝ - ማየት ቀልቤን እንደሳበው ሁሉ የኩራት ክብር በዓልም ቀልቤን ምናልባትም በዕኩል ደረጃ ነው የሳበው።**

አላውቅም እና ራሴን በሚያዋርድ ሁኔታ ውስጥ አስቤው አላውቅም። ስለዚህ በማንነቴ እንድኮራ ኩራት በዐል ላይ ተማርኩኝ ማለት አልችልም። በቃ ራሴን ነኝ፣ እስካሁን ያልገለጽኩት መሳብ ለሴት ያለኝና ከዚህ በኋላ ልተገብረው የሚገባኝ። ከአሜሪካዊ የክፍል ጓደኞቼ በተለየ ሁኔታ እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ ወሲባዊ ፍላጎቴ ምን እንደሆነ በ18 ዓመቴ ዐለማወቄ ጉዳዬ ሊባል የሚችል አልነበረም።

ወደ ኩራት አብሬያቸው የሄድኩት ጓደኞቼ ይኽ የኩራት በዓል የመጀመሪያዬ እንደሆነ ስለሚያውቁ ተንከባክበውኝ ነበር። በተመሳሳይ ዕድሜ ላይ ያለን ቢሆንም አብዛኛዎቹ በቀደሙት የኩራት በዓላትን ታድመው የሚያውቁና ሊሆን የሚችለውን ሁሉ የሚያውቁ ናቸው። እኔ ምኑም ዕውቀቱ አልነበረኝም። የኢንተርኔቱ አቅረቦቱ ባልነበረበት፣ የማኅበራዊ ትሥሥር አማራጮች ጨርሶ በሌሉበት ሁኔታና እንደ አንድ አዲስ አበባ እንዳደገ ሰው ለኩዊር ባህል ፍጹም ሩቅ ነበርኩ።

ኩራት ድሮ ድሮ ክብረ በዓል ከመሆኑ በላይ ለተግባር ጥሪ ማድረጊያ ነበር፤ እናም በቀለም ያሸበረቁ የቡድን ዝማሬዎች ይሰሙበት ነበር። “ሄይ ሄይ ሆ ሆ ተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ጠልነት መወገድ አለበት” ሠልፈኞቹ ጮክ ብለው እየደጋገሙ የሚያሰሙት ዝማሬ ነበር። እየተቀባበሉ የሚያሰሙት ዝማሬን አስታውሳለሁ “ምንድን ነው የምንፈልገው? ዕኩል መብት፤ መቼ ነው የምንፈልገው፤ አሁን” እና “2፣ 4፣ 6፣ 8 ተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪነት እንደ ተቃራኒ ፆታ አፍቃሪነት መልካም ነው።” የማያውቁት ዓይነት የደስታ ስሜት ይፈጥራል። አብዛኛው በግልጽ ወጥቶና ከሌሎች ተመሳሳይ አቋም ከሚያራምዱት ጋር በመሆን ራሳቸውን ይህን ዓለም ለመጪው ትውልድ የተሻለ ለማድረግ የተሰጡ ነበሩ።

ስለዚህ ዐለፍ ብዬ ቁጭ ብዬ የሚሉትን መድገም ጀመርኩ “ሄይ ሄይ ሆ ሆ ተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ጠልነት መወገድ አለበት”። ታዳጊና በግልጽ ለመውጣት አዲስ የሆንኩ ተመስሳይ ፆታ አፍቃሪ ነበርኩ፤ ዕኩለ-ቀን ላይና በነገሩ ማብቂያ ላይ ግን በርግጥም ይህ የኔ ነገድ እንደሆነ ግልጽ ሆነልኝ። ከማንም የማይሆን አስተያየት ለመቀበል ከማይፈቅዱ፤ ከላይ ልብሳቸውን ካለበሱ ተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ሴቶችና ሃይለኝነት ከሚነበብባቸው “drag queens” ባጠገብ ደ’ሞ ዐለፍ ብለው “እነዚህ ሁሉ ኩዊር ሰዎች ቀጥታ ሲዖል ነው የሚገቡት” ከሚለው የፀረ- LGBTQ ደጋፊዎች ሰበካ የገባኝ፤

ወደ ቤቴ እየመጣሁ እንደሆነ ነው።





# መብረር

## በውስጥ ያለን የአርነት ሰንደቅ ዐላማ ማውለብለብ

የኩራት ቀን (Pride) አንድነትን፣ "አለን" ብሎ መታየት እና የሰብዓዊ መብት ትግል ቀጣይነትን የምናስታውስበት ቀን ነው። በዚህ ቀን ላይ ኩዊር ቤተሰቦች ብቻ ሳይሆኑ ሰብዓዊ መብት ይመለከተኛል ለሚሉ ደጋፊዎችም አንድነታቸውን የማሳያ ቀን ነው። በሁለትዮሽ ስርዓተ ፃታ ላይ የሚራመደውን አለም የተለያየ ወሲባዊነት እና ስርዓተ ፃታ ማንነቶች መኖራቸውን በቦታ በመገኘት የምናሳይበት እና የምንከባበርበት ቀን ነው።

በድረ ገፆች ላይ የተለያዩ ፍቅረኛሞችን ፎቶዎች የማይበት፥ ያላወቅኳቸውን የፐራይድ ታሪኮች የማነብበት እና ይበልጥ ደግሞ ማህበራዊ ሚዲያው በህብረ ቀለም ደምቆ የማይበት ጊዜ ስለሆነ ደስ ይለኛል።

ለአንድ የኩራት ቀንን አይደለም ማንነቷን ለብዙ አመት ቋንቋ ላጣችለት ወጣት የኩራት ቀን ምንድን ነው? እንደኢትዮጵያዊ እና በጥብቅ ክርስትና ሀይማኖት እንዳደገ ሰው ቀኑ እና የኩራት ወር ምን ጥቅም አለው?

በቤተክርስቲያን ውስጥ "የከፉ ስራ ነው" እና ከዛም ውጪ ደግሞ "የኢትዮጵያዊ ባህል አይደለም" እየተባልኩ ነው ያደኩት። ምንም እንኳን ለሌላ ሴት ተማርኮ እንዳለኝ ያወቅኩት በጣም በልጅነቴ ቢሆንም ሀጢያት፣ ከባህል ውጪ እና ስህተት እየተባልኩ ማደጌ ከራሴ ጋር ትልቅ ጦርነት ውስጥ ከቶኛል። ክርስቲያን እና ሌዝቢያን አብረው የማይሄዱ ማንነቶች እንዳልሆኑ ራሴን ነግሬ ለብዙ አመት የሌዝቢያን ማንነቴን ደብቄ ኖሬያለሁ። ኢንተርኔትም ላይ ቢሆን ስለሌዝቢያን ማንነት እንጂ ክርስቲያን እና ሌዝቢያን በሚል ለማንበብ ጥረት አላደረኩም። ምክንያቱም አብረው አለመሄዳቸው እንደ "ወተት ነጭ ነው" አይነት ግልፅ ነበር። ኩዊርነቴን ለመቀበል ጊዜ የወሰደው ትልቁ ነገር ከክርስትናዬ ጋር ማስታረቅ መከበዱ ነው።

በ20ዎቹ አጋማሽ ላይ ራሴን ከማወቅ ወደመቀበል ስመጣ ነው ኩዊር እና ክርስትና አብረው መሄዳቸውን ለማንበብ ድፍረቱን ያገኘሁት። አለም ላይ ያሉ የተለያዩ ቤተ እምነቶችን አየሁ

> ምንም እንኳን ፕራይድ የሚከበረው ባህር ተሻግሮ ቢሆንም ተመሳሳይ ማንነቶቻችን ያስተሳስሩናል፡፡ በተጨቆነ ማህበረሰብ ውስጥ የኲዊር ሰዎችን ደስታ፣ ትግል እና ፈሽታ ማየት እንደመፈታት ነው፡፡

ከዛ ውስጥ በጣም የደነቀኝ በደቡብ አፍሪካ ያሉ ቤተ እምነቶችን ማየቴ ነው። ብዙ ጊዜ ያላችሁ መረጃ ከአፍሪካ ውጪ ሲሆን ግንኙነቱን ያርቀዋል። የደቡብ አፍሪካው ቤተእምነት አጠገቤ ያለ ነው የመሰለኝ። ብዙ አነበብኩ፣ ያላቸውን ነፃ አጫጭር መረጃዎች አነበብኩ። ለዘመናት የደበቃችሁትን ወይም ለመምረጥ የተገደዳችሁትን ማንነት ሰዎች በነፃነት ሲኖሩት ማየት እጅግ ደስ ይላል። “ሀጢያተኛ” እያለ የሚወቅሰውን ህሊና ያስታግሳል።

ለኔም “ኲዊር ክርስቲያን” የሚለው ማንነት ጉዞ የጀመረው በእንዲህ አይነት መንገድ ነው። እንደኢትዮጵያዊ የኩራት ወር ባይኖረንም የኩራት ጉዞዬ ማንነቶቼን የሚያጣምሩ እንዲህ ያሉ “አለን” የሚሉ ድህረ ገፆችን ማግኘት ነው። ባንዲራ በከተማዬ ማውለብለብ ባልችል እንዲህ አለን የሚሉ መረጃዎች ውስጤ ያለውን ባንዲራ በየቀኑ እየረዘመ እንዲውለበለብ ያደርጉታል።

ቤተ ክርስቲያኖች “ወሲባዊነትን የመመለስ ህክምና” በሚል በአለም ዙሪያ ያሉ ብዙ ሺ የሚቆጠሩ ኲዊር ሰዎችን አደጋ ላይ ጥለዋል። ይህም በእኛ ሀገር በፀሎትና ፀበል ተቃራኒ ፃታ አፍቃሪ ለመሆን ብዙዎቻችን የሞከርናቸው ድርጊቶችን ያካትታል። እነዚህ ቤተ ክርስቲያኖች “ህክምና” በሚል ስም ጥላቻን ይበልጥ በመስበክ ብዙዎችን ለተለያየ የአዕምሮ ህመም አጋልጠዋል። ታዲያ እንደዚህ አይነት ቤተ-ክርስቲያኖች ባሉበት አለም ላይ ይሄንን የሚቃረኑ፣ የፈጣሪ ቤት ለሁሉም ክፍት ነው፣ ፈጣሪ ለሁሉም ፍቅር ነው የሚሉ ቤተ እምነቶችን ማየት እንዴት አያስደስትም?!

ቤተ ክርስቲያን የሰበከችውን የዘመናት ጥላቻ እነዚህ ቤተ ክርስቲያኖች ለእንደኔ አይነቱ ሰው እውነተኛ ህክምና ናቸው። ኢትዮጵያ ውስጥ በጥላቻ ተከቦ እንዲህ አይነቱን ውጤት የሌለው “ህክምና” እንዲሁም ጥላቻን ሁልጊዜ አጥብቀው የሚቃወሙ ቤተ ክርስቲያናትን ማየት ያበረታል።

ከእንደዚህ አይነት የማንነት ማስታረቅ ቀጥሎ ነበር የፕራይድ በዓልን በደማቅ ሁኔታ የመካፈል ገጠመኞችን ያገኘሁት። የፕራይድ በዓልን መካፈል ለኔ መንፈስን ያድሳል። ለብዙ አመት የብቸኝነት ስሜት ሲሰማኝ እና ይሄ ስሜት ያለኝ ብቸኛ ሰው እኔ ነኝ ስል ኖሬ በአንድ ትልቅ ጎዳና ላይ ከተለያየ የአለማችን ክፍል ከመጡ ኲዊር ሰዎች ጋር መገናኘት ስሜቱን እንዴት መግለፅ ይቻላል?! ለራሴ ጮክ ብዬ እንኳን ስለማንነቴ መንገር ባፈርኩበት እንደገና ኩሩ ከሆኑት የኲዊር ቤተሰቦች ጋር መገናኘት እንደመዳን ነው የምቆጥረው። በበዓሉ ላይ በክርስትና እምነት ውስጥ ሆነው አገልጋይ የሆኑ፣ ተጋብተው የሚኖሩትን ማየት ነፍስን ያድሳል። የተከለከልኩት ነገርን ሁሉ በብዙዎች ማየት እንዴት ደስ አይል?!

እነዚህ የፕራይድ ወራት ትልቅ ትርጉም አላቸው። ምንም እንኳን ሁሉ አብሮ ለማክበር እድሉ ባይኖርም እንዳለሁ እንኳን በማልቆጠርበት ሀገር ላይ ሌላም አለም እንዳለ ይመሰክሩልኛል።

የኲዊር ሰዎች ደስታ እና ድምቀትን ማየት ይሄም ይገባናል፣ ይቻላልም ያስብለኛል። በሚያሳዝን መልኩ የብዙዎቻችን ታሪክ የሚጀምረው ከራስ ትግል ነው ስለዚህ ነፃነትን ማየት ካሉብን የረዥም አመት የስሜት ቀውስ ውስጥ ተስፋን ይጭራል፣ ጥንካሬን ይሰጣል።

ምንም እንኳን ፕራይድ የሚከበረው ባህር ተሻግሮ ቢሆንም ተመሳሳይ ማንነቶቻችን ያስተሳስሩናል። በተጨቆነ ማህበረሰብ ውስጥ የኲዊር ሰዎችን ደስታ፣ ትግል እና ፈሽታ ማየት እንደመፈታት ነው።

ፕራይድ እንደትውስታም እንደፈውስም ነው። ጥቁር እና ክርስቲያን ሆነው ለዛሬ ነፃነቴ በተለያየ መልኩ የታገሉ ብዙዎችን ያስታውሰኛል፣ ድፍረታቸው እና ጀግንነታቸው ይበልጥ ያነሳሳኛል። ነገ የተሻለ ነው ያሰኘኛል። ራሴን እንዳከብረው ያስተምረኛል።




# የፕራይድ አጀማመር

የ"ኩራት" ወር ብለን የምንጠራው በሰኔ 21 ቀን 1961 ዓ.ም. የተከሰተው የ"Stonewall riots" ወይም ዐመፅ መታሰቢያ ነው። ዐመፁ የተጀመረው ፖሊስ ያልተጠበቀ ጥቃት በኒውዮርክ በሚገኘው Stonewall Inn በተባለው ቡና ቤት ላይ በመፈጸሙ የተቆጡ LGBTQ+ የቡና ቤቱ ደንበኛ ባደረጉት ተቃውሞ ነው። በኒውዮርክ ያሉ የLGBTQ+ ማኅበረሰብ በፖሊስ እጅ የሚደርስባቸውን ያልተጠበቁና ጭካኔ የተሞላባቸው ጥቃቶች ለብዙ ዓሥርት ዓመታት በጽናት ዐሳልፈዋል፤ ብዙም ተጎሳቁለዋል።

ምንም እንኳን የLGBTQ+ ሰዎች የሙብት ትግል ከStonewall Riots (ዐመፅ) የቀደመ ታሪክ ቢኖረውም፤ ዐመፁ የ"ጌ"ዎችን የነፃነት ትግል አዲስ ዐቅም ሰጥቶታል።

የክብረ-በዓልነትና የተቋውሞ ባህሪያትን ደርቦ የያዘው የመጀመሪያው የኩራት በዓል የተካሄደው ሰኔ 11 ቀን 1962 ዓ.ም. በኒዮርክ ከተማ ነው። ይህ ክብረ-በዓል እንደምሳሌነት የሚያገለግል ነው፤ እና በቅርቡ የኩራት ትዕይንተ ሕዝብ በዓለም ደረጃ ተሥሥርቷል።

አሁን ኩራት ሁሌም በየዓመቱ ሰኔ ላይ የሚካሄድ ዓለም ዐቀፍ ክብረ- በዓል ሆኗል።

ኩራት የክብር በዓል ክፍል ነው። ማኅበረሰቡ አንድ ሆኖ ለLGBTQ+ ለሆኑ ሰዎች ፍቅሩን፣ ወዳጅነቱን እንዲሁም ጊዜውን በመስጠት ኩራታቸውን በግልጽ ለማሳየት እንዲችሉ ማድርግ ያለበት ጊዜ ነው። ያም ብቻ አይደለም ስለLGBTQ+ ሰዎች ሕይወት፣ ተሞክሮ እና ታሪክ በግልጽ መነጋገርን ጭምር ማበረታታት ያለበት ጊዜ ነው። ኩራት LGBTQ+ የሆኑ ሰዎችን ሙብት ለመጠየቅ የሚደረግ ተቃውሞ ጭምር ነው። ለትግሉ የበለጠ ድጋፍ በማድረግ የLGBTQ+ ሙብት በዓለም ዐቀፍ ደረጃ እንዲከበር ለማድርግ ጊዜው አሁን ነው።

LGBTQ+ ለሆኑ ሰዎች ሙብት በዓለም ዐቀፍ ደረጃ ለመሟገት ትዕይንት ሕዝቦች እና ኮንስርቶች ይከናወናሉ። LGBTQ+ የሆኑ ሰዎች በሚጎሳቀሉባቸው በዓለም ላይ ባሉ አንዳንድ ቦታዎች ሰዎች ክብር-በዓሎቹን በድብቅ ያከናወናሉ፤ ራሳቸውን የደኅንነት ችግር ውስጥ እየከተቱ እንደሆነ ዕያወቁም ይሣተፋሉ።

---

*"ታሪክ ወደኋላ መለስ ብለን የምናየው ነገር አይደለም ... ታሪክ ወደ ኋላ ተመልክተን የማይቀር ነበር የምንለው ነገር አይደለም፣ የሆነበት ምክንያት ሰዎች አንዳንድ ጊዜ በጣም ግልፍተኛ እና ቅጽበታዊ የሆኑ ውሳኔዎችን ስለሚያደርጉ ነው፣ ነገር ግን እነዚያ ወቅቶች የተጠራቀሙ እውነታዎች ናቸው።"*

ማርሻ ፒ. ጆንሰን

(እ.ኤ.አ በ1969 ዓ.ም. በተካሄደው የstonewall አመፅ ውስጥ ታዋቂ ከሆኑት መካከል አንዷ የነበረችው አሜሪካዊት የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪያን ነጻነት አራማጅ)

---







“ . . . በዛ ቀን መስቀል ዐደባባዩ ብገኝ ሊደርስብኝ ከሚችለው በላዩ አለመገናቱ የሚያመጣብኝ ነገር አስፈራኝ። ”









# የራሴ የግል መስቀል አደባባይ

ሥጋት የተጫነው ተሞክሮ ነበር። ሊይዙን ቢችሉ ምን ሊያደርጉን እንደሚችሉ ልገምተው ሁላ አልቻልም። እኔና እኔን የምትደግፈኝ ሰው መስቀል ዐደባባይ ላይ የLGBTQI+ ማኅበረሰብ አባል ሊያሰኘን የሚችለውን ምልክት ይዘን በመቆማችን ሊገጥመን የሚችለውን አደገኛ ሁኔታ በደንብ ነበር የማውቀው።

ዕቅዱ ቀላል የሚባል ነበር። አብሮኝ ላለ ሰው "የኩራት በዓል" እየደረሰ እንደሆነና ለሁለታችንም የሚስማማ ጊዜ ማመቻቸት እንዳለብን አስታውሰዋለሁ። ከዛም ከመስቀል ዐደባባይ የሚፈለገውን ያህል ርቀን እንቆማለን፤ ቦታና ማዕዘን መርጠን ግርግሩ እስኪቀንስ እንጠብቃለን። በመቀጠል ፊቴን በወረቀት እሸፍነና እሷ ፎቶ ታነሳኛለች። ይሄው ነው! የግሌ የአንድ ሴት የኩራት በዓል!

> **ኩራት በመንግሥትና በፖሊስ በሚደርስባቸው ከፍተኛ መንገላታት የተንገፈገፉ ኒዎርካዊያን ቁጣ የወለደው ተቃውሞ ነበር።**

የፍርኅታችን መነሻ ቀላል አልነበረም። አንድ በLGBTQI የተጠረጠረ ሰው ዕጣ-ፋንታው ምን ሊሆን እንደሚችል ይገባኛል። ያም ሆኖ ግን በዛ ቀን መስቀል ዐደባባይ ብገኝ ሊደርስብኝ ከሚችለው በላይ አለመገኘቱ የሚያመጣብኝ ነገር አስፈራኝ። ኢትዮጵያ ውስጥ ኩዊር ሆኖ መኖር መታፈን ማለት ነው፤ እያንዳንዷን ቀን በትንሽ በትንሹ ስሞት ይሰማኛል። የመነጠል ስሜቱ ይታከተኛል፣ ሁል ጊዜ መፍራት፣ ኩዊርነት ላይ ከሚነሳው ተቃርኖ ጋር በየጊዜው መጋፈጥ፣ መደበኛ የሕይወቴን ሁነቶች መደበቅ..... ምን መጽሐፍ እንደማነብና ከማን ጋር የፍቅር ጊዜ እያሳለፍኩ እንደሆነ፣ የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ጠልነት አሰለቸኝ፣ እንደ አንድ ሥርዓተ-ፆታን በተለየ መልኩ እንደሚተገብር ሰው በአዲስ አበባ ጎዳናዎች ላይ መሄድ የሚፈጥርብኝ የፍርኀት ስሜት አደክሞኛል እናም ሁል ጊዜ ሁላችንም ላይ የሚኖርብን ፍላጎት የተቃራኒ ፆታዎች ብቻ ነው መሆን ያለበት; የሚለው ተጠባቂነት እጅግ ያስቆጣኛል፤ በተለይ እንደሴት።

ነፃ መሆን እፈልጋለሁ፤ ማመፅ እፈልጋለሁ፤ መታገል እፈልጋለሁ።

እናም የአንድ ሴት የኩራት በዓል የትግል መንገዴ ነበረች። ለምን ኩራትን የትግል መድርክ ማድረግ ፈለኩ?

ኩራት ዝም ብሎ ፌሽታ ሆኖ አያውቅም። ኩራት ትልቅ ዐመፅ ነበር፤ ኩራት ሥልጣንን መታገያ ነበር፤ ኩራት መቃወሚያ ነበር። ኩራት በመንግሥትና በፖሊስ በሚደርስባቸው ከፍተኛ መንገላታት የተንገፈገፉ ኒዎርካዊያን ቁጣ የወለደው ተቃውሞ ነበር።

ኩራት ዝም ብሎ በባዶ ሜዳ የተከሰተ ነገር አይደለም። በምዕራቡ ዓለም ያሉ የLGBTQI ማኅበረሰብ ለዓመታት ተዘጋጅተውበታል። የመጀመሪያው የተሠነደ የጌ መብት ተቋም፣ የሰብዓዊ መብቶች ማኅበረሰብ የተመሠረቱት በ1916 ዓ.ም. ነበር። የአሜሪካ የመጀመሪያ

“ **መስቀል ዐደባባይ ላይ የአንድ ሴት የሆነችው ኩራት ዳግም ለመተንፈሴ ምክንያት ነበረች። ለመታየትና ለመቆጠር የተደረገ ጥረት ነበር።**

የሌዝቢያን ሴቶች መብቶች ተቋም፣ እንዲሁም የቢልጌት ሴት ልጆች ተቋማት የተመሠረቱት በ1947 ዓ.ም. ነበር። የStonewall Riots በመባል የሚታወቀው ሕዝባዊ ዐመፅ ዝም ብሎ በባዶ ሜዳ የተፈጠረ አልነበረም። የትግሉ መንፈስ ስኬታማ የሆነበት አንዱ ምክንያት የተቀናጁ በመሆናቸውና ማኅበረሰብ መገንባት በመቻላቸው ነበር። እንደዚህ ዓይነት ማኅበራዊ እንቅሳቃሴ በአንድ ቀን አይገነባም እናም Stonewall Riots የተሰኘው ዐመፅ የትግል መንገድ ስላሳየን ብዙ ተጠቅመናል። ያም ብቻ አይደለም እንደኲዊር ሕይወታችንን በከበበው በኢ-ፍትሐዊነት ላይ ብርታት ሆኖናል፤ ምክንያቱም አሁን መደራጀትና ተራማጅ ማኅበረሰብ መመሥረት ሁሉን እንደሚያስችል አሳውቆናል።

በዚህም የተነሣ የተለያዩ የኲራት በዓላት ላይ ተገኝቻለሁ። በአንድ ትንሽዬ ከተማ ከ100 ያነሱ ሰዎች በነበሩበት ሠልፍ ተሣትፌያለሁ፤ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች የተሣተፉበት ሠልፍ ላይም እንዲሁ ተሣትፌያለሁ። በተጨማሪም ማኅበራዊ ፍትሕ እንዲሰፍን ከሚጠይቁ በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ጋር ተሰልፌያለሁ ። ያም ብቻ አይደለም ሌሎች ሠልፍ ሲያደርጉ አለፍ ብዬ ቁጭ ብዬ ዐይቻለሁ።

ምንም እንኳን ኲራትን እንደንግድና ለተወሠኑ ሰዎች የተሰጠ ወደመምሰል መምጣቱ ቢያሳዝነኝም፤ ሁሌም መደበቅን፣ በተፅዕኖ ሥር መውደቅን  እና ዝም ማለትን የሚቃወም መልዕክትን ከያዙት ጋር ነው የቆምኩት። በተጨማሪም ኲራት የተወሠነ የጋራ ነገር ካለኝ ኲዊሮች ጋር የጠበቀ የቤተሰብ ስሜት እንዲኖረኝ ያደረገም ተሞክሮ ነው። ኲራት ለኔ በጎዳናው ላይ ኃይል የሚሰጠኝ ነው፤ ለአንድም ሆነ ለሁለት ቀን “ኖርማል” የምንሆንበት ቀን ነው፤ መደበኛ ተሸካሚዎች።

መስቀል ዐደባባይ ላይ የአንድ ሴት የሆነችው ኩራት ዳግም ለመተንፈሴ ምክንያት ነበረች። ለመታየትና ለመቆጠር የተደረገ ጥረት ነበር። በኢትዮጵያ ያለን ኲዊሮች አንታወቅም፤ ለኛ በብቸኝነት ድምፅ የሚሆኑን ወይ የምዕራቡ ዓለም ካልሆነም ደ’ሞ በምዕራቡ ዓለም ያሉት ናቸው።

ይህ በተግባርም ኢትዮጵያ ውስጥ ላለነው ጭምት እንድንሆን ምክንያት ሆኗል፤ ጥቁርና ሴት  ባናቱም ከታዳጊና ደኻ ሀገር በመሆናችን ብዙ ጊዜ ለመናገር እየፈለግን ጎታች ሆኖብናል። በዚህ ምክንያት LGBTQ+ መሆን በሞት ከሚያስቀጣበት ቦታ የመጣን ሰዎች የተወለድንበትን ሀገራችን ጥለን መሄድ እንመርጣለን ወይም እንገደዳለን። ስለዚህ መስቀል ዐደባባይ መቆም ማለት እንደኲዊር ሴት የትውልድ ቦታዬን የማስመለስ ጉዳይ ብቻ ሣይሆን መስቀል ዐደባባይን እንደ ማክበሪያና መታገያ ቦታ ያለው ዋጋ ለመናገር የሚኖረኝን ውሣኔ ከሚመጣብኝ ጣጣ በላይ ያጠናክርልኛል። ራሴንም ሆነ ፎቶ የሚያነሣኝን ሰው እዛ ቦታ ላይ በመገኘታችን ምን ዓይነት ጣጣ ውስጥ እንደከተትኩኝ በደንብ ይገባኛል፤ ያም መናገሬን የበለጠ ኃያል ያደርገዋል።

እስካሁንም መስቀል ዐደባባይ ላይ ፊቴን ሸፍኜ ምልክቱን መያዜ ያን ያኽል ጀግንነት ሊባል የሚችል መሆኑን ዐላውቅም፤ የማውቀው የፊት መከለያዬን ባወርደውና ፊቴን ባሳይ የበለጠ ጀግንነት ይሆን እንደነበር ነው። ያ ግን ራሴ ላይ ጋዝ አርከፍክፌ በእሳት እንደማቃጠል ቢሆንም ፤ ከዛ ባነሰ ደግሞ እንድ LGBTQI+ የኛ መገለጫ የሆነውን ምልክት መስቀል ዐደባባይ ላይ ይዤ የሚኖረኝ ፎቶም ቀጣዩ ምርጥ የጀግንነት ተግባር ነበር።

ይህ ነበር የኔ Stonewall riot. የግሌ የመስቀል ዐደባባይ ዐመፅ፤ ከፍተኛ ጥላቻና አደጋን ተጋፍጬ የማደርግው ትግሌ።

እናም፤ በመጨረሻም አንድ ቀን አካታችና ተራማጅ የኲዊር ማኅበረሰብ ፈጥረንና በኢትዮጵያ ውስጥ ተባብረን ኲራታችንን በራሳችን የሕይወት መንግድ በየቀኑ ማሳየት እንድምንችል ተስፋ ሰጠኝ። በግልጽና በኲራት!




*Gilbert Baker preserved this 10- by 28-foot section of an original 1978 pride flag. (GLBT Historical Society / Courtesy of Andrew Shaffer)*

# የቀስተ - ደመና ሰንደቅ ዐላማ ታሪክ

የቀስተ-ደመና ሰንደቅ ዐላማ በአሜሪካዊው የጥበብ ሰው፣ የንድፍ ሃሳብ አወጪ ባለሙያና “drag performer” በሆነው ጊልበርት ቤከር በ1970 ዓ.ም. ተፈጠረ። ለሳንፍራንሲስኮ ዓመታዊ የኩራት ትዕይንት ሕዝብ ላይ እንዲያገለግል በሚል ባንዲራውን የመፍጠር ተልዕኮ የተሰጠው፤ በአሜሪካዊው ፖለቲከኛ ሀርቬይ ሚልክ ነበር።

ከሁለት ዓመት በፊት የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ሴትና ወንድ መገለጫ የሆነው ባንዲራ ጉዳይ በቤከር ጭንቅላት ውስጥ ይመላለስ ስለነበረ፤ እሱን ለመምረጥ መወሰኑ ትክክል አጋጣሚ ነበር። ቤከር በ2007 ዓ.ም. ከMuseum of Modern Art ጋር በነበረው ቃለ-መጠይቅ ላይ እንደተናገረው፤ በ1968 ዓ.ም. ሁለት መቶኛ ዓመቱን በደፈነው አሜሪካን እንደነፃ ሪፐብሊክ መፈጠሯን የሚዘክረውንና የአሜሪካንን ዐብዮት የሚያስታውሰው ክብረ-በዓል ላይ በተደጋጋሚ ባለኮኮብና መስመር ምልክት የያዙ ተዕይንተ ሕዝብ ማስተዋሉ፤ ተመሳሳይ ባህል ለተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪያን ማኅበረሰብም ያስፈልገዋል የሚል ሃሳብ ፈጥሮበታል። የራሱን አልባሳት በመፍጠር እንደሚታወቅ “drag performer”ቱ፤ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጎላ የመጣውን ምልክት ለመስፋት በሚገባ አስችሎታል።

በጊዜው፤ በስፋት ጥቅም ላይ ሲውል የነበረው የ”ጌ” መብት እንቅስቃሴ ምልክት  ባለሦስት ማዕዘን ሮዝ የነበር ሲሆን፤ ምልክቱ በናዚዎች “ሆሞሴክሹዋሎችን” እንደ’መለያ ሆኖ አገልግሏል። ለባከር እንድዚህ ዓይነት ጨለማና አሳዛኝ ትዝታዎችን ትቶ ያለፈ ምልክት ምርጫው ውስጥ ሊገባ የሚችል ጉዳይ አልነበረም። ከዛ ይልቅ ቀስተ-ደመናን ነበር ስሜቱን በተሻለ ይግልጽልኛል ብሎ የመረጠው።

ባንዲራው ላይ የሚታዩት ኅብረ-ቀለማት የ“LGBT” ማኅበረሰብ አባላት ከሁሉም ዘር፣ ዕድሜ ክልልና ፆታ ውስጥ እንደመምጣታቸው መጠን አንድነትን ይውክላሉ ተብሎ በመታሰቡ፤ እንዲሁም ቀስተ-ደመና ተፈጥሮዓዊና ቆንጆ በመሆኑ  ነው። የባንዲራው ዋና ቅጂ ባለስምንት ቀለማት ሲሆን ሁሉም የተለያየ ትርጉም ያዘሉ ናቸው። ከላይ ያለው ደማቁ ሮዝ ወሲብን ሲወክል፣ ቀዩ ሕይወትን፣ ብርቱካናማው ፈውስን፣ ቢጫው ፀሐይን፣ አረንጓዴው ተፈጥሮን፣ የሰማያዊና የአረንጓዴ ቀለማትን ባህሪ የሚጋራው ጥበብን፣ ጥቁር ሰማያዊው መዋሃድን/ስምምነትን፣ በመጨረሻም ከታች ያለው ሃምራዊው ቀለም ስሜትን ይገልጻል።

ምንጭ: https://www.history.com/news/how-did-the-rainbow-flag-become-an-lgbt-symbol

# አጋርነት

## “ኖርማልን” በድጋሚ ፍቺ መስጠት

በሦስተኛ ዓለም ሀገራት፤ ልክ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ እየኖሩ፤ አባሪ መሆን ማለት ምን ማለት እንደሆነ ሁሌም ግራ ይገባኛል። በርግጥ አንድ ሰው የ”LGBTQ+” ማኅበረሰብን ኑሮ የተሻለ ለማድረግ ምን ማድረግ ይችላል? ጨርሶ “ሆሞፎቢክ” በሆነ ማኅበረሰብ ውስጥ ተሁኖ እንዴትስ ተብሎ ነው ለLGBTQ+ ማኅበረሰብ ፍትሕ መቆም የሚቻለው? ሰዎችን በማንነታቸውና ለፍቅር በሚፈቅዱት ምርጫቸው ምክንያት ሥጋት ላይ እንዲወድቁና ሕይወታቸው ለአደጋ እንዲጋለጥ በሚሆንባት ሀገር ላይ፤ እንዴት ተብሎ ነው ራስና ሌሎች በማኅበረሰቡ ከሚጫን አስከፊ ተፅዕኖ መጠበቅ የሚቻለው? እነዚህን ጥያቄዎች የምመልስበት ቀላል መንገድ የለኝም። በርግጥም እጅግ በጣም ከባድ ነው። በተለይ እኔ ባደኩበት ማኅበረሰብ ውስጥ፤ ያም ሆኖ ግን አንድ ነገር ርግጥ ነው፤ ፀቡ፣ ትግሉ ለቅቡልነት፣ ለዕኩልነትና ለመሠረታዊ ሰብዓዊ መብቶች ነው።

ይሄ ሳይረሳ የኔ አብሮነት መሠረቱን ያደረገው በማዳመጥና አብሮ በመሆን ላይ ነው። ቁጣንም ያካትታል፤ ሊኖር የሚገባን ጥሩ ሕይወት ስለማጣት፣ በቂ የጤና አጠባበቅ አቅራቦት ስለማጣት፣ የሥራ ዕድል፣ ከሁሉም በላይ ግን ራስን ለመሆን ዕድል መንፈግ። ሰዎችን ሰብዓዊ የሆኑ መብቶቻቸውን መንፈግ እጅግ ኋላ ቀርነት ነው። የLGBTQ+ ማኅበረሰብን ወደ ኋላ መመለስና ወደተለምዷዊ ስርዓት ፆታ የሕይወት ዝንባሌና ተቃራኒ ፆታ አፍቃሪነት መመለስ ይቻላል ብሎ ማመን በዓለም ላይ ሊቀር የሚገባ ነገር ነው። ወደ’ኋላ መመለስና መስተካከል ካለበትም በራስ የሕይወት ተሞክሮ ላይ ተመሥርተን ይኸ ነው ትክክሉ ብለን መበየንና ሰዎችን ትክክል ነው ብለን ባሰብነው ሣጥን ውስጥ ማስቀመጥ ነው፤ እሱ ነው መቀየር ያለበት።

በዚህና በሌሎች ምክንያቶች ኩራት ለማበር አስፈላጊ ነው። ኩራት እንደ ማበሪያነት ለኔ በጣም አስፈላጊው ነገር ነው። ምክንያቱም በየዓመቱ አዲስ ነገር እማርበታለሁ። ኩራት ከ”Stonewall Inn raid” ጀምሮ የLGBTQ+ ማኅበረሰብ ያስገኛቸውን ሥኬቶች ማክበሪያ ነው። ያም ብቻ ሣይሆን ያልተሠሩ ሌሎች ብዙ ቀሪ ሥራዎች እንዳሉም የምናስታውስበት ነው፤ በተለይም ፖሊሲዎችንና ሕጎችን ለመቀየር ሥልጣኑ ያላቸው ሰዎች አሉ፤ የሰዎችን ሕይወት ከባድ ለማድረግ የማይታክቱ። በተጨማሪም ለኩዊር መብት ደጋፊዎችም መማሪያ ነው፤ ቦታው ላይ ለመሆንና ለመደገፍ፤ ድምፅ ለመሆን። ድምፅ መሆን ሲባል መናገር ማለት ነው። ሰውን በወሲባዊ ማንነቱ በሚያጎሳቁል ማኅበረሰብ ውስጥ ይህን ማሰቡ ከባድ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን የደረጃ በደረጃ ሂደት ነው፤ በማዳመጥና ቦታው ላይ በመገኘት የሚጀምር፣ አብሮነቱ በኢ-ፍትሐዊነት ፊት በእውነተኛነት ወደ መቆም ማደግ አለበት። ስለሆነም ምኞቴ ነው፤ እያንዳንዱ ኩራት የበለጠ ደፋር፣ ድምጿችንን የምናሰማና ጠንካራ እያደረጉን እንደሚመጡ፤ ምክንያቱም ከምንም ነገር በላይ ተጋድሎው የ ለዕኩልነትና ለመሠረታዊ የሰብዓዊ መብቶች ስለሆነ። አይደለም እንዴ?

> “
> [አጋርነት] የደረጃ በደረጃ ሂደት ነው፤ በማዳመጥና ቦታው ላይ በመገኘት የሚጀምር፣ አብሮነቱ በኢ-ፍትሐዊነት ፊት በእውነተኛነት ወደ መቆም ማደግ አለበት።



# በሕይወት ዘመናችሁ "ኩራት" እንደ ክብረ በዓል በኢትዮጵያ ውስጥ ሲከበር የምታዩበት ጊዜ የሚመጣ ይመስላቹኃል?

አይ! አይ! በኔ ዕድሜ የሚሆን አይመስለኝም። በልጆቼ ዕድሜ የሚሆን አይመስለኝም።  በልጅ ልጆቼም ዕድሜም እንደዛው።  ስቀልድ ነው። ምናልባትም 85 ዓመቴ ላይ ስደርስ እንደዛ የሚመስል ነገር ለፈጠር ይችላል። ምክንያቱም ብዙ ኢትዮጲያዊ ወዳጆች አሉኝ እዚህ ሀገር ያሉና እዚህ የሚኖሩ። እናም ከነሱ ጋር ስናወራ በጣም የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ጠልነት ነው ያለው።

ምንም እንኳን የተራማጆች እንቅስቃሴ ቢኖርም፤ በአንጻሩ ግን ያለው አስተሳሰብ ተመሳሳይ ነው፤ ምንም አልተቀየረም። የተለያዩ መረጃዎች አሉ። እናም ራሴን እጠይቃለሁ፤ በርግጥ ሰዎች እያሰቡት ያለው አስተሳሰብ ላይ ለውጥ ለማምጣት ምን ማድረግ ይቻላል? ምን ማድረግ ይቻላል? መልሱ ቀላል አይደለም።

በንጉሥ ኢዛና፤ ክርስትና ወደ ሀገራችን ከገባበት ጊዜ ጀምሮ በአንድ ወይም በተመሳሳይ ርዕዮት-ዓለማዊ አስተሳሰብ ነው ያለፍነው። በጣም ከባድ ነው እና ብዙ ማስወገድ ያሉብን ነገሮች አሉ፤ ብዙ መሥራት ያሉብንና መመለስ ያሉብን ጥያቄዎች አሉ። ያን ልናደርግ ከምንችልበት አንዱ መንገድ ምናልባት ሚዲያ ላይ በመሥራት ነው። ያ ሊሆን የሚችለው ግን ከኢትዮጵያ ሣይሆን ከዚኽ ተሁኖ ነው።

ኢትዮጵያውያን ተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪነትን ከምዕራባዊነት (ከነጭነት) ጋር ያገናኙታል፤ ከዛ ድ`ሞ ኢትዮጵያውያን ተመሳሳይ አፍቃሪ ነን ሲሉ ታማችሁ ነው ይሉናል። ኢትዮጵያ ውስጥ ሆነን ያለምንም ከልካይ ኃይል ምን ያኽል ሥራ ልንሠራ እንደምንችል አላውቅም። ስለዚህ ዲያስፖራው ይኽን ኃላፊነት መውሰድ እንዳለበት እገምታለሁ። ገባሽ፤ በግልጽ ወጥቶ "እኔ እንደማንም ዓይነት ሰው ነኝ፤ እኔ እነዚህን ነገሮች አላደርግም፤ ጓደኛኽ ነኝ፤ ቤተሰብሽ ነኝ፤ የምታውቀኝ ሰው ነኝ" ማለት አለበት ብዬ እገምታለሁ። እንደዚህ ዓይነት ሥራ ነው የሚያስፈልገን። እና እናንተ (ኩዊር ኢትዮጵያ) የምትሠሩት ሥራም እንዲሁ በጣም አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም እናንተ የምታጋሩት ታሪክ የሌላውም ሰው ታሪክ ነው፤ ሌላው የሚጋራውን ነገር የሚያገኝበት። ሰው አንብቦ "ይኽ ስሜትኮ እኔም ጋር አለ" የሚልበት። የኢትዮጵያ ኩራት በዓል ላይ ለመገኘት በጣም እፈራለሁ። ድሮኖች



ከላያችን ሆነው ሊጠብቁን የሚችሉበት መሆን አለበት፤ እንዳንሞትና እንዳንገደል ማለት ነው።

ቀልድ አይደለም! ብዙ የተዛባ መረጃ ስላለ እንደዚህ ዓይነት በዓላት ላይ ሰዎች ቁጡ ናቸው። በማኅበረሰባችን የ"ፀረ-ጌ" አጀንዳ በባህሉና ልማዱ ውስጥ ሥር ሰዷል። እናም በምን አይነት ስራ መንቀል እንደምንችል አላውቅም።

**"**

**የኢትዮጵያ ኩራት በዓል ላይ ለመገኘት በጣም አፈራለሁ። ድሮኖች ከላያችን ሆነው ሊጠብቁን የሚችሉበት መሆን አለበት፤ እንዳንሞትና እንዳንገደል ማለት ነው።**



“

**እዚህ [ከኢትዮጵያ ውጭ] ሆኖ ኩራትን ከመሣተፍ የበለጠ ዕውቅና ነው። የተወለድኩበት ቦታ ነው።**

ሊሆን የሚችል ይመስለኛል። ምን ያኽል ጊዜ እንደሚወስድ ግን ርግጠኛ አይደለሁም። የሚሆን ከሆነ ግን፤ ቢያንስ፤ ምናልባት በጥቂት ዓመታት ውስጥ ይሆናል። ተስፋ የማደርገውን ነው፤ ያው መልካሙን በማሰብ ነው፤ አላውቅም ብቻ። ለረጅም ጊዜ በሕግ ከልክለውት የቆዩ ሀገሮች ነበሩ፤ በኋላ ግን በሕግ የፈቀዱት፤ ስለዚህ የመንግሥት መቀየር ያን ያመጣ ይሆን? ለዛም ምን ያኽል ጊዜ እንደሚወስድ አላውቅም።

በጣም ትልቅ ትርጉም ይኖረዋል። እናም በርግጠኝነት የምገኝበት ይሆናል። ትልቅ ዕውቅና ነው የሚሆነው። እዚህ ሆኖ ኩራትን ከመሣተፍ የበለጠ ዕውቅና ነው። የተወለድኩበት ቦታ ነው። አለ አይደል ሁለት ማንነቶቼ እርስ በርስ ሲስማሙ ነገር።

እንደዚህ ዓይነት በዐል ይኖራል ብዬ የማላስበው ቦታ ነው። ትልቅ ደስታ ነው የሚሆነው።

“

**ዕውቅና ለማግኘት በርካታ ዓመታትን ይጠይቃል።**

ግልፅ በሆነ መንገድ የሚካሄድ አይሆንም። በአንድ የዳሰሳ ጥናት ላይ እንዳነበብኩት ከሆነ ኢትዮጵያ ውስጥ 97% የሚሆነው “LGBTQ+” ማንነቶችን ይቃወማል። በጥናቱ ላይ በመቶኛ የተቀመጠው ቁጥር እንዲህ በአጭር ጊዜ የሚቀንስ ይሆናል ብዬ አላስብም። ዕውቅና ለማግኘት በርካታ ዓመታትን ይጠይቃል። ተጋድሎ እስካላደረግንና ዝም እስካልን ድረስ፤ ኩራትን ሳናከብር የሚያልፉትም ጊዜያት በዛው ልክ እየረዘሙ ይሄዳሉ።

“

**ራሴን ሙሉ በሙሉ ለመግለጽ ቀላል የሚሆንልኝ አይመስለኝም።**

እኔ ከልቤ ቢቻል ብዬ አጥብቄ እመኛለሁ። ከሀገሬ የለቀኩት ስድስት ዓመቴ እያለ ነው። ነገር ግን ስምንት ዓመቴ ሲሆን ተመልሼ ሄጃለሁ። እዛ ካሉ ቤተሰቦቼም ጋር ያለኝ ግንኙነት የተጠበቀ ነው። እዛ ያለው አሁናዊ አጠቃላይ ሁኔታ ዕውቀቱ አለኝ ብዬ ባላስብም ነገር ግን ከተለያዩ ፀረ-LGBTQ+ነትን ከሚያራምድ ኃይማኖታዊነት ጋር መጣበቃችንን መገመቱ አይከብድም። በዚህ ላይ ደሞ የምንኖርበት ዓለም ወንዳዊነት እና አጠቃላይ ከብሔርተኝነት ጋር ያለው ነገር ሲደመርበት፤ ይመስለኛል እነዛን ማንነቶች አደገኛ ሁኔታ ውስጥ ለማስገባት ሁኔታውን የተሟላ ያደርገዋል። ስለዚህ እንደማስበው፤ እስካሁን በሰማሁት በጣም ምቾት ይነሳኛል፤ ኢትዮጵያ መሄዱ በራሱ። ራሴን ሙሉ በሙሉ ለመግለጽ ቀላል የሚሆንልኝ አይመስለኝም። አዎ! ግን ደግሞ ይኽ አስተያየት ዓሥር ዓመት ርቆ በኖረ ሰው የተሰጠ አስተያየት መሆኑ መረሳት የሌለበትም።

# በህይወት ዘመናችሁ ኢትዮጵያ ውስጥ የኩራት ክብረ በዐል ሲከበር የምታዩ ይመስላችኋል?

---

እነዚህ ምላሾች ከፌስቡክ ገፅ የተወሰዱ ናቸው ...

---

**Bonnie Fufa**
እውነት ለመናገር በኔ የህይወት ዘመን የማይ አይመስለኝም:: opposite sex date ሚያደርገው ራሱ expect ሚደረገው to get married without dating ነው:: i am not sure the society is familiar with the concept of love yet.

**Mes Robel**
በእኔ የሕይወት...ኋላቀርነቱንና ድንቁርናውን 😏
በኃይማኖትና በባህል ስም ሸፍኖ መኖርን ምርጫው ያደረገ ትውልድ ባለበት ድግሱ የሚታሰብ አይመስለኝም ባይሆን በሕይወት እያለሁ ተመሳሳይ ፆታ ያላቸው ተፋቅረው ማየትን በጥቂቱም ቢሆን ማህበረሰቡ እየለመደው የሚመጣና ተካብዶ የሚወራ ጉዳይ መሆኑ የሚቀር ይመስለኛል 😊

**Khaled Kala**
እንደ እኔ በመጀመሪያ ፕራይድን ከማሰባችን በፊት እኛና ማህበረሰባችን ያለበት ሁኔታ ምን ይመስላል የሚለውን ቆም ብለን ማየት ያለብን ይመስለኛል የኛ ችግሮች እራስን ካለመቀበል ጀምሮ ለራሳችን እና ለሌሎች ክብር ያለመስጠት በመካከላችን ያለመዋደድ ያለመተሳሰብ እነዚህና መሰል ችግሮች ማህበረሰባችን ውስጥ ጎልተው ይታያሉ እና እነዚህ ነገሮች ባሉበት ፕራይድን ማሰብ ከባድ ይመስለኛል በመጀመሪያ እኛን እና ማህበረሰባችን ( LGBTQ) የሚመጥን አቋም ሊኖረን ይገባል እኛ የተፈጠርነው ለ SEX ብቻ ሳይሆን ለፍቅር ለጓደኝነት ለስኬት ቤተሰብ ለመመስረት በአጠቃላይ ትልቅ ለሆነ ማንነት እንደሆነ በማመን ሁሌም ለራሳችን ከፍያለ አመለካከት ሊኖረን ይገባል
ሁሌም ከሀይማኖት አባቶች እና ከማህበረሰቡ የምንሰማው እኛ የምናደርገው ነገር ሃጥያት እንደሆነና ፈጣሪን የሚያስቆጣ እንደሆነ ነዉ ሲጀመር እንዴት ነዉ ጌታችን ከዚህ ስሜት ጋር ፈጥሮን ሲያበቃ ሀጢያት ነዉ የምትሰሩት እያሉ የሚነግሩን ወይስ ፈጣሪ ሰዉን ሲፈጥር ስህተት ይሰራል ማለት ነዉ?
ሁላችንም የምንስማማበት ነገር ፈጣሪ በፍጹም ስህተት እንደማይሰራ ነዉ ስለዚህ ጓደኞቼ ለምንድነው ሁሌም እራሳችንን እንደጥፋት የምናየው ለምንድነው ለራሳችን ስሜት ክብር የማይኖረን ሂወት በጣም አጭር ናት ትክክለኛ ውሳኔዎችን መወሰን ለምን ይከብደናል? እኔ አንተ አንቺ ለምን በማንነታችን እናፍራለን? ለምን እራሳችንን አንቀበልም? ለምን በራሳችን አንኮራም?
ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ ሲኖረን ያኔ በ ኢትዮጵያ ውስጥ ፕራይድ እውን መሆን ከባድ አይሆንም በኔ የህይወት ቆይታ ያንን የማየት እድል ቢኖረኝ በጣም ደስ ይለኛል ቀጣዩ ትውልድ ስለ ፆታዊ ማንነት (gender identity) የተሻለ awareness ይኖረዋል የሚል እምነት የለኝ::

**Nahi Gay**
እኛ ሀገር ላይ እማይ አይመስለኝም የሆነ ተአምር ተፈጥሮ እንኳን ቢከበር ህዝቡ ዲንጋይ እና ዱላ ይዞ ሚያባርረን ነው ሚመስለኝ ያለው ጥላቻ ከባድ ነው አንዴ ከቤተሰብ ጋር ስለኛ ጉዳይ ወሬ ተጀምሮ የተሰጡትን አስተያየቶች ሳስባቸው ይከብዱኛል ከተሰጡት የመፍትሄ ሀሳቦች መሀል አንዱ ሰብስቦ ማቃጠል እሚለው ነበር አሁን ድረስ ሳስበው ጆሮዬ ላይ ያቃጭላል እንደው ይሄን ፍርድ ከፈረዱባቸው መሀል አንዱ እኔ የነሱ የቤተሰብ አባል እንዳለው ቢያውቁ እንዲ ይሉ ነበር ብዬ ሳስብ ደሞ
አንዳንዴ ከሀገር የመውጣት ፍላጎቴ በድንገት ሚጨምረው ለዚ ይመስለኛል አንድ ቀን ግን ከሀገር ውጪ ካሉ መሰሎቼ ጋር እማከብር ይመስለኛል Proud Gay እሚል ቲሸርት ለብሼ በቀኝ እጄ ደሞ ባንዲራችንን ይዤ እና ምወደውን ቆንጆ አጭር የጅንስ ቁንጣ አርጌ 👭👬❤️

# ድምፅ አልባ እውነቶች

አመንክዮ ቀርቶ ለምን ባይ ሲጠፋ ፥
ተጠፈጥሮ ከደንቦች የግዱን ሲጋፋ ፥
ነፍሳችን ከያዛት እውነት ስትላፋ ፥
የደረቡላትን ራሷን ያለመሆን ካባን ለማሽቀንጠር ፥
ብዙ ትርቃለች ደቦ ካፀደቀው ቅቡል አፈጣጠር ፥
ይሄን ግዜ ታድያ ዓለም ይከሳታል ፥
ሀቅን የነጠፉ ጭፍንፍን ሀሳቦች ያንከራትቷታል ፥

ጥበብ በጎደለው ዕውቀት ባነሰበት ፥
ድርሳናት ተገልጠው ባላዋቂ አንደበት ፥
ሰማይና ምድርን ያፀናውን ትተው ፥
ሰዎች ፈራጅ ሆኑ ሰውነትን ረስተው !

በሀይማኖት ሰክረው እምነትን ሲቀብሩ ፥
በህግ ሲከለል የነፃነት አፀድ የማንነት ክብሩ ፥
ከነፍሳችን ደጃፍ በጥላቻ ደምቀው ይቆሙና ፊቷ ፥
ቀለሟን ማወቋን ይሉታል ሀጥያቷ !

ይህ ሁሉ ቢሆንም

መርጠን ባልመጣነው ማንነት ተገፍተን ፥
ከህብረ ቀለም መሐል የኛን ቀለም ሰርተን ፥
በረሳን ዓለም ውስጥ ሌላ ዓለምን ፈጥረን ፥
በአንድ አይነትነት ደዌ ሳንመታ ዙርያችንን አጥረን ፥
ዛሬ ላይ ቆመናል አንድነት ደግፎን ፥
ያልተቀበሉልን ማንነት አግዝፎን ፥
ዋጋ የከፈልንለት እውነታችን አቅፎን!

ከማስመሰል ህይወት ከውሸት ሰመመን ፥

ሀጥያት ያሉት በሽታ ፥

የእውነት እስከኖርን ግዴለም ይመመን !